# ዳግም መታለል ጥፋቱ የማነው?

ከአዳነች መኮ (ቫንኮቨር፤ ካናዳ)

የግንቦት ሰባቱን ድል ሶስተኛ ዓመት መታሰቢያ በምንዘክርበት ወቅት፣ ባለፉት ጥቂት ወራቶች ብዙ ጥያቄዎች በተለያዩ የስብሰባ መድረኮች፣ ፎረሞች እና ቃለመጠይቆች ተነስተው ከሀቀኛ ታጋዩም፣ ከታማኝ ተቃዋሚውም፣ ከቅጥረኛውም የተለያዩ ነገሮችን ሰምተናል። ማን ምን እንደሆነ፣ እውነትና ሀቅ ከማን ጋር እንደሆነ በቂ ግንዛቤ እንዳልተገኘ ሁሉ፤ ዛሬም ያንኑ ዘፈን ከፊትና ከኋላ ሽፋኑንና ቀለሙን እየቀያየሩ ከማቅረብ በቀር ሁለቴ ሶስቴ የሚታለል ሕዝብ የለምና ይህንን እውነታ ማሳወቅና ድብቅ ተልእኳቸውን በየጊዜው ማጋለጥ ያስፈልጋል።

የወያኔን እድሜ ለማራዘሚያ ውስብስብና የተለያዩ ዘዴዎችን ቢጠቀሙም መሰረታቸውን ካወቅን ዘንዳ በተደጋጋሚም መጃጃል እንደሌለብን ለማስገንዘብ ነው የዚህ ጽሑፍ ዓላማ።

የዛሬ ሶስት ዓመት እነ ብርሃኑ ነጋ ምን ሰሩ? እነ ልደቱ ምን ሰሩ? እነ በየነ ጴጥሮስ ምን ሰሩ? ብሎ መጠየቅ የትላንትና ክህደታቸውና ወንጀላቸው በዛሬ የተቀነባበረ ዘዴ ተዘንግቶ ትግሉን በድጋሚ ለውጭ ጠላቶችና ለወያኔ መገበር የለብንም። ሕዝብን የከዳ ከሃዲ ነው። መሳሳትና መክዳት የሰማይና ምድርን ያህል ልዩነት አለው። እነ ብርሃኑ ነጋ ከነቪኪ ሃድልስን ጋር የሸረቡት ምን ነበር? እነ ብርሃኑ ነጋ ቃሊቲ እስር ቤት እያሉ ከእስር ቤት እጽ እንደሚያስነግዱ ማፍያዎች ውጭ ካሉ ቅጥረኞቻቸው፣ ከእነ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ብርሃነ መዋ፣ ሞገስ ገብረማርያም ወዘተ ጋር የተቀጣጠለውን የሕዝብ ትግል ነጥቀው የትግሉ ደጋፊ የከፋፈሉ ያዳከሙና የትግሉን አቅጣጫ ያሳቱ መሆናቸውን ጨርሶ መዘንጋት የለበትም።

ለመሆኑ እነ ብርሃኑ ነጋ በመጠኑም ቢሆን አደገኛና አሳሳች መንገዶቻቸው ብዙውን ኢትዮጵያዊ እንዲበሳጭ፣ ተስፋ እንዲቆርጥና እንዲከፋፈል ቢያደርጉም፤ እውነት ደግሞ በተራዋ ወጥታ ትክክለኛውን የትግል አቅጣጫ ለማሳየት በመቻሉ፤ የሕዝቡን ትግል መልሶ አቅጣጫ ለማስያዝ ብዙ አድካሚና ከፍተኛ ርብርቦሽ እየተደረገ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ማን እንደከዳው ማን ምን እንደሆነ ስላወቀ በገንዘብ ኃይል ሊያታልሉት ቢሞክሩም አልተበገሩም። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የሞቱለት፣ የቆሰሉበት፣ የተደበደቡበት፣ የተሰደዱበትን ትግል እነ ብርቱካን ሚዴቅሳ፣ እነ ብርሃኑ ነጋ፣ እነ አንዳርጋቸው ጽጌ ሊነግዱበት አይችሉም።

ዛሬ ቅንጅትን አስረክበው ሌላ ፓርቲ መስርተናል እያሉ እነ ብርቱካን ሚዴቅሳ ሲቀልዱብን፤ አራዳው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ደግሞ አንዴ "ኮሌክቲቭ ሊደርሽፕ" ሌላ ጊዜ ደግሞ እኔ ግራ ገብቶኛል ትግሉ ምን መሆን እንዳለበት ብሎ ሕዝብን ግራ ሲያጋባ፤ ሌላ ጊዜ በቅንጅት ስም ሲነግድ አሁን ደግሞ ከቅንጅት ወጥተናል ብሎ አረፈው። ግልግል። አሁን ደግሞ ከኒውዮርክና ከዲሲ በሪሞት ኮንትሮል ትግል ሊያካሂድ፣ ካስመራ ጦር ሊያንቀሳቅስ እየተዘጋጀ መሆኑን ተናገረ። ለመሆኑ እርሱ ነው እንዴ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አቅጣጫ የሚወስነው? ዋሽንግተን ዲሲ ካሉ ጓደኞቹና የውጭ ቅጥረኞች ጋር ሰላለሳ ነገር ሲቀባጥር ይሰማል። ብርሃኑ ነጋ የነበረከት ስምዖን ጓደኛ ውጭ አገር ለመቅረት የፈለገበት ዋናው ምክንያት በውጭ ያለውን ትግል ለማኮላሸት ነው። የሕዝብን አደራ የተቀበለና ኃላፊነት የሚሰማው ሰው የሚያደርገውን ሳይሆን በተግባር እያደረገ ያለው፤ ሴራውና ተንኮሉ ስለተነቃበት በብስጭት በየሬስቶራንቱ ከመጠን በላይ ሲጠጣና ሰክሮ ሲወላገድ፣ እንደጎረምሳ በየናት ክለቡ ሲጨፍር ያለን ሰው የትጥቅ ትግል እመራለሁ ሲል የሚከተል የተጃጃለና ማመዛዘን የማይችል ብቻ መሆን አለበት። በሀያ ዓመቱ ሸሽቶና ጥሎት የሄደውን ትጥቅ ትግል በሃምሳ ዓመቱና ባለሃምሳ ሚሊዮን ብር ቱጃር ሲሆን ያደርገዋል ብሎ ማሰብ መጃጃል ነው። ብርሃኑ ነጋም ሆነ ብርሃነ መዋ በአገር ቤት ብዙ ሚሊዮን ብር የሚንቀሳቀስ ንብረታቸውን የሚነካባቸው የለም ለምን? እንዴት ነው አሜሪካና ለንደን ተቀምጠው ጦር እንዲሰብቁ የተፈቀደላቸው? ረጋ ብሎ ማሰብ ይጠይቃል። ዛሬ ዳግም መታለል ጥፋቱ የብርሃኑ ሳይሆን እርሱን አምኖ ለመታለል ፈቃደኛ የሆነው ክፍል ነው።

እዚህ ቫንኮቨርና ሲያትል ያላችሁ ከስብሰባችሁ በኋላ ብርሃኑ ነጋ አራዳ መሆኑንም ሳትዘነጉ ጥሩ ናይት ክለብ ይዞ የሚሄድ አንድ አጃቢ ጎረምሳና አጃቢ አነስታዮች አዘጋጅታችሁ ማስጨፈሩን አትርሱ። አለበለዚያ የትጥቅ ትግሉ አይሰምርማ! እንዲህም አድርጎ ትግል የለም።